# በህገ-መንግስታዊ መብቶች ሽፋን ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን የመናድ ከንቱ ምኞት

(ክፍል 2)

ዮናስ 01/10/14

ነጻው ፕሬስን ጨምሮ የመንግስት ሚዲያው፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ በአስተምህሮ ደረጃ የሃይማኖት ተቋሞች ሳይቀሩ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የማይናቅ ሚና ያላቸው ስለመሆኑ የዘርፉ ልሂቃን የሚስማሙበታል፡፡ ያለእነዚህ ተቋማትና ስብ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉም ባይሆኑ የሚበዙቱ በተለይም የ97ቱ ቅንጅት ሌላኛው ገጽታ የሆነው መድረክ የኋልዮሽ ከመጓዝ እና እንቅፋት ከመሆንም አልፎ ስርአቱን ከመሰረቱ ለመናድና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሀይል በማስወገድ ከቀድሞው ለከፋ ስርአት ሃገሪቱን በማጋለጥ ላይ የመሆኑ ነገር ነው አጀንዳዬ ።

ይኸውም ምንም እንኳን በቀጥታ የሽብር እንቅስቃሴ ውስጥ አብዛኞቹን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተሳትፎ ባንመለከትም በተለይም በምርጫ 97 ቅንጅትና ህብረት የተባሉት ፓርቲዎች የደረሰባቸውን ሽንፈት ላለመቀበልና ከተቻለ በምርጫ ካልተሳካም በቀለም አብዮት ስልጣን መያዝ የግድ መሆኑን አስቀድመው ባቀዱት መሰረት ለመፈጸም ያደረጉት ሙከራ ባለመሳካቱ ባሳለፍነው 8 አመታት ውስጥ የተለያዩ አጋጣሚዎችን እና ግርግሮችን በመጠቀም ያደረጉት የቀለም አብዮት ሙከራ በህገመንግስታዊ መብቶች ሽፋን የተደረገ ነው ፡፡

ይህን ተከትሎ የሰሜን አፍሪካውን የአረብ አብዮት እንደጥሩ አጋጣሚ የወሰዱትና ለዚህም አበክረው የሰሩት ሃይሎች በተለይም የቅንጅት ርዝራዦችን ከያሉበት አግበስብሶ እና ሌሎችንም መነሻና መድረሻ የሌላቸውን ሃይሎች ሰብስቦ ያቀፈው መድረክ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃይማኖት ስም ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ አክራሪ ሃይሎች ጋር ስለቀለም አብዮት ጋብቻ መፈጸሙና ይህንንም ለመፈጸም ህገ መንግስቱን ሽፋን ማድረጉ ይታወሳል ፡፡

በዚህም የተነሳ ለመታሰራቸው ምክንያቱ "የገዥው ስርአት ፍራቻና ስለፍርሃቱም ያወጣው የፀረ ሽርተኝነት አዋጅ ነው" በማለት መከራከራቸውና የአደባባይ ላይ ግርግሮችን

ማስነሳታቸውም የቅርብ ጊዜ ታሪካቸው መሆኑ ይታወሳል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ መድረኩ ስለቀለም አብዮት ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ ከተሸነጠበት መንደር ፣ ከዛም እንደመድረክ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ መስራቱና የ"አልሰራሁም" ትርክቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአሸባሪነት ጋር ያደረገውን ያልተቀደሰ የጋብቻ ገመና ያጋለጠ ክስተትም ተፈጥሮ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ይኸውም አልሸባብ የተሰኘው አሸባሪ ቡድን ጥቅምት 3/2006 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከናይጀሪያ አቻው ጋር ለአለም ዋናጫ የመጨረሻማጣሪያ ጨዋታ በሚያደርግበት እለትና የኢትዮጵያ ህዝብ ነቅሎ በየአደባባዩ በወጣበት ሰዓት የተከናወነ ነው፡፡

አሸባሪ ቡድኑ በኬኒያ የንግድ ማእከልና በዩጋንዳ የኢትዮጵያ ሬስቶንት የደረሰውን አደጋ አዲስ አበባ ላይ ለመድገም ቢሞክርም ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል እንዲሉ እራሱ ላይ በማፈንዳት ሴራው የተጠናቀቀ መሆኑን አንዘነጋም ፡፡ ኃላፊነቱንም አሸባሪ በድኑ መውሰዱን በገዛ ድረ ገጹ የመሰከረና የድረ ገጽ ባለሙያዎችም የአልሸባብ መሆኑን ማረጋገጣቸው አይረሳም፡፡

ዳሩ ግን የመድረኩ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ግለሰብ "ገዥ ስርአቱ እራሱ አጥምዶ እራሱ በለመደው ሁኔታና ለለመደው ግርግር የፈጠረው እንጂ አሸባሪዎች አይደሉም፤ አሸባሪነት የኢትዮጵያ ስጋት አይደለም" ሲሉ በግልጽና በህዝብ ሚዲያ ላይ ሳይቀር መናገራቸው ነው የመድረኩንና የአሸባሪዎችን ያልተቀደሰ ጋብቻ የገለጠው። አሁንም ወደ ኋላ ተመልሰን በህገ መንግስታዊ መብቶች ሽፋን ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን ለመናድ የተደረጉ ሙከራዎችን እናንሳ፡፡

የሙስሊም ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የከሰሩ ፖለቲከኞች መድረኩ ህዝበ ሙስሊሙን አነሳስቶ ወደ ግጭት ያስገባልናል ያሉትን ስልት ሁሉ መጠቀማቸውን እናስታውሳለን፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ቀደም ሲል ሲደርስበት የነበረውን በደል በማራገብና በመቀስቀስ ከ ዚህም አልፎ ተገቢነት የሌላቸው አዳዲስ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለማነሳሳትና ለማተራመስ ሲሰሩ ማየትም የተለመደ ነው፡፡

በትምህርት ቤቶች መስጊድ እንዲሰራ ደጋግሞ በመወትወት ሃይማኖትና ትምህርን ለመነጣጠል የተቀመጠውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ለመጣስ ጥረት አድርገዋል፡፡ በአንድ ወቅት እነ መድረክና ተወካዮቻቸው በህዝብና ቤት ቆጠራው ላይ የተገኘውን ተጨባጭ

ውጤት የአሜሪካን ስለላ ድርጅት ያለአንዳች ጥናት ሲያስተጋባው ከነበረው ቁጥር ጋር በማነፃፀር የሙስሊሙን ማህበረሰብ ሆን ተብሎ ለማሳነስ የተደረገ ተንኮል አስመስለው ማቅረባቸውንም አንዘነጋውም፡፡

በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የሚካሄዱ ግጭቶችን የመቀስቀስ ሙከራዎች በቃልና በፅሁፍ ብቻ የተወሰኑ ከመሆን አልፈው ወደተግባርም የተሸጋገሩት በመድረኩና መሰል ፓርቲዎች እንደነበርም አይዘነጋም፡፡ ሼህ ኑር ሁሴን  የአክራሪዎች ሰለባ በነበሩ ጊዜ መድረኩ “መንግስት ያቀነባበረው ነው” ሲል ማላከኩንም አንርሳ፤ ይህ አይነቱ አካሄድም አክራሪነትን የት ሊያደርሰው እንደሚችል ስጋታችንን መግለፃችን አይረሳም።

 ይህ ብቻ አይደለም፤ መድረክና መሰሎቹ በዜጎች ላይ የህይወት ጉዳትን፣ በንብረት ላይ ውድመትን ከማስከተላቸውም በተጨማሪ ያለመረጋጋትና የስጋት ድባብ እንዲያጠላብን አድርገዋል፡፡ በአንድ አካባቢ የተፈጠረን ግጭት እንደሰበብ በመጠቀምም የበቀል እርምጃ እንዲወሰድ በመገፋፋት፣ ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ እንዲወጣ ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉም ቆይተዋል፡፡

 በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች አልፎ አልፎ ከተቀሰቀሱትና በአጭር  ከተቀጩት ግጭቶች የበለጡ ብዛት ያላቸው ውጥረቶች ወደግጭት ሳይሸጋገሩ እንዲረግቡ በመደረጉ እንጅ እንደ አክራሪዎቹ  ሙከራና እንደመድረኩ ጠንካራ ምኞት  ቢሆን ኖሮ ከዚህም የባሰ ግጭትና ደም መፋሰስን በተመለከትን ነበር፡፡

ሃይማኖትንና ጎሳን ሽፋን በማድረግ የሚካሄዱ ግጭቶች ወይም ግጭት የማነሳሳት ሙከራዎች በተለያዩ ደረጃዎች የሚታዩና አሉታዊ ውጤት የሚኖራቸው መሆኑ አይቀርም፡፡ ግጭቶች በትንሽ በትንሹ ብቻ የሚከሰቱ ከሆነ ምን ጊዜም ቢሆን የስጋት መንፈስ መፍጠራቸውና ተጨባጭ ጉዳት ማስከተላቸው አይቀርም፡፡ ትንንሽ የሚመስሉ ነገር ግን ደግሞ በየእለቱ የሚደጋገሙ የግጭት ክስተቶች በህዝብ ላይ ከባድ ስነልቦናዊ ተፅእኖ ያሳርፋሉ፡፡ አንዱ ግጭት ለሌላ ግጭት መቀስቀስ በር እየከፈተ ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ሊያደርጉም ይችላሉ፡፡ በዚሁ ልክ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት የጠፋበት አገርና ህዝብ መስለን እንድንታይና ገፅታችን እንዲበላሽም ያደርጋሉ፡፡

ከነዚህ ትንንሽና የማያቋርጡ ግጭቶች ባሻገር እንደመድረኩ ምኞት በነጻ ፕሬስ፣ በሰብአዊ መብቶች እና በመሳሰሉት ህገ-መንግስታዊ መብቶች ሽፋን ሃይማኖትንና ጎሳን እየነካኩ የሚቀሰቅሱ ግጭት ሲኖሩ ደግሞ ለበርካታ ህይወት መጥፋት፣ ለከፍተኛ ንብረት ውድመትና በህዝባችን መካከል በቀላሉ የማይበርድና ለቀጣይ ግጭትና ፍጅት በር የሚከፍት የጥፋት መንገድ ይከፈታል፡፡

በዚህ ያላበቃውና ያላፈረው መድረክ ይባስ ብሎ አዲሱ ፕሬዝዳንት በበዓለ ሲመታቸው ያሰሙት ንግግር ላይ ሞሽኖችን ተቀብሎ ለማጽደቅ በተሰየመው ም/ቤት ላይ በተወካዩ አማካኝነት አሸባሪነትን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ቀላቅሎ በማቅረብ ህዝብን ለማደናገር ያደረገው ሙከራም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ሙከራውም በተመሳሳይ ሳይሳካ በአብላጫ የተቃውሞ ድምጽ ውድቅ ቢሆንም ጉዳዩን በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማርያም ደሳለኝ ከሰጡት ማብራሪያ ከአጀንዳዬ ጋር ተያያዥ የሆነውን እና ከመድረኩ ገመና መጋለጥ ጋር የሚያያዘውን ነጥብ ብቻ እናስታውሳለን፡፡

የአልሸባብ ዋና አላማና ታርጌት ኢትዮጵያ ስለመሆኗና ለዚህም ሲባል አሸባሪ ቡድኑ በዙሪያዋ ማኮብከቡንና የቡድኑ አንድ ክንፍ የሆነው የእስልምና ፍ/ቤቶች ህብት መጀመሪያ ጂሃድ ያወጀው ኢትዮጵያ ላይ መሆኑን በማስታወስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ አሸባሪ የሆነው የአልሸባብ ክንፍ በይፋ በአገራችን ላይ ጂሃድ ባወጀበት ወቅት ስሩን ለመንቀል የተደረገውን ዘመቻ በቅድሚያ በወከላቸው የህዝብ ወንበር ላይ ተቀምጠው የተቃወሙትም ሆኑ የመግለጫ ጋጋታ ያሰሙት ዛሬ በመድረክ ጥላ ስር ያሉትና አመራር በመሆን ከሰሞኑ የሰልፍ ተከለከልን መግለጫ በማውጣት የተጠመዱት ሃይሎችመሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል ፡፡

የአሸባሪ ቡድኑ ተጋላጭ እና ኢላማ ከሆኑትና የአሚሶምን ጦር በማዋቀር የአሸባሪ ቡድኑ መነኻሪያ ወደሆነችው ሶማሊያ ከዘመቱት አገራት ኢትዮጵያ ግንባር ቀደምና ከዘማችነትም ያለፈ የመሪነት ሚና ያላት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ከማጠናከር አንጻር ኢትዮጵያ አሁንም የመሪነት ሚናን ወስዳ እቅድ በማውጣት ከሃገራቱ ጋር ከመግባባት ላይ መድረሷም በጠቅላይ ሚንስትሩ ተመልክቷል ፡፡ በዚህ አግባብ ከኋላ የተከተሉት ኬንያና ኡጋንዳ ላይ አልሸባብ እንዲህ ከተመጻደቀ ለኢትዮጵያ ደግሞ ታላቅ የሞት ድግስ አዘጋጅቶ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

ከፀረ ሽበር ትግሉ ፈተናዎች ደግሞ የከፋው በህጋዊና በሰለጠነ ትግል ስም፣ በተለይም በህገ መንግስታዊ መብቶች ሽፋን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሃይል ለመናድ በተንሸዋረረ እና ህገ ወጥ መንገድ  የሚንቀሳቀሱ መድረክን የመሰሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው፡፡

አክራሪነት በአገራችን የተፈጠረ ሳይሆን አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ባህሪ ያለው ጸረ ዲሞክራሲያዊ ተግባር ነው፡፡ ጉዳዩም የአፍሪካ ቀንድና ሰሜን አፍሪካ የሚቸገሩበትና የሚፈተኑበትም እየሆነ ነው፡፡ ስለዚህም ነው የመጨረሻ ግቡ አሸባሪነት የሆነውን አክራሪነት ህዝቡን ባለቤት በማድረግ መንግስት ግልጽ አቋም ይዞ እየታገለው የሚገኘው፡፡

በሃይማኖት ስም  የሚደረግ  አክራሪነት ካለ መጀመሪያ መታገል ያለበት  ምእመኑ ነው፡፡ ምነው ቢሉ? ጉዳዩ ሃገር ማጥፋትና ስልጣን ብቻ ሳይሆን ሽፋን የሆነውን እምነትና ሃይማኖትም እጅጉን ስለሚጎዳ ነው፡፡ የሃይማኖት እኩልነት፣ የእምነት  ነጻነት የተከበረባት አገር፣ የፕሬስ ነጻነትም ሆነ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ የተረጋገጠባት፣ የቡድንም ሆነ የነጠላ የእምነት ነጻነት የተከበረባት አገር እንዲኖረን ካስፈለገ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገ ትግልና እርምጃ የግድ ያስፈልገናል፡፡

የመድረኩ አመራሮችና  ከአሸባሪነት የፖለቲካ ትርፍ የሚሹ ሃይሎች አክራሪዎች የሚያደርጉትን ፀረ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ አስመልክተው መነሻው *መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱ ነው* የሚለውን ህገ መንግስታዊ መብት ሽፋን ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡ የሰዎችን  የእምነት ነፃነት መጻረር፣ የኔን ካልተከተልክ ብሎ ድብደባና ግድያ ከማከናወን በላይ ህገ-መንግስት መጣስ የለምና፣ ጉዳዩ የሃይማኖት እኩልነትን፣ የእምነት ነጻነትን ያጎናጸፈውን  ህገ መንግስታዊ ስርአት የመናድ ተግበር ነው። ህግ የማስከበርና ህገ መንግስቱን የመጠበቅ  ሀላፊነት ያለበት መንግስት ይህንኑ ሲሰራ “ጣልቃ  ገብቷል” ብሎ መከራከር  ሊበሏት ያሰቧትን ጅግራ ስለሚሆን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለመናድ ከማቆብቆብ  ተለይቶ አይታይም፡፡

እነዚህን ትዝታዎች ይዘን ሰሞንኛ የሆኑትንና በተቃውሞ ሰልፍ፣ በፕሬስ ነፃነትና በሰብአዊ መብቶች ህገመንግስታዊ ሽፋን የተደረጉ ጨዋታዎችን ስንቃኝ ቁማሩ ግልጽ ይሆንልናል።

በእርግጥ እነዚህ የፖለቲካ ቁማርተኞች *የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ተከለከልን* ዜማቸው በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሔዱ ባሉ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ላይ ቢያፌዙም አስቀድሞም ቢሆን *ተከለከልን* ስለሚፈልጉትና ጮኸው ሊያጫጩኹበት ስለሚሹ እንጂ

አማራጭ ቦታዎች ተዘጋጅቶላቸው እንደነበር በሁሉም ዘንድ ይታወቃል። መስቀል አደባባይን ጨምሮ በርካታ ቦታዎች በመንገድ ግንባታና በባቡር ፕሮጀክት መያዛቸው ግልጽና የሚታይ ሃቅ ሆኖ እያለ፣ በርካታ ኀዳናዎች አማራጭ የትራንስፖርት መስመሮች መሆናቸውም እየታቀወቀ፣ ታላቁን ሜዳና ብዙዎችን ማስተናገድ የሚቻለው ጃልሜዳን "ቁርጠኛ ታጋይ ነን" የሚሉት እነዚሁ ሃይሎች በሙጃና በማይመስሉ የህፃናት ማሳበቢያ መንገዶች እንቢኝ ማለታቸውም እንዲሁ የማይዘነጋ የቅርብ ጊዜ ሁነት ነው።

ነተቃራኒው፣ ከመድረኩ ውጪ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በቀረበላቸው አማራጮች በመጠቀምና (ምንም እንኳን በኋላ አላማቸው ሌላ እንደሆነ እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ እንደሆነ ከላይ በተመለከተው አግባብ ግልጽ ቢሆንም) ህገመንግስታዊ መብታቸውንም መሰረት በማድረግ በአንድ ወር ውስጥ ከአምስት ያላነሱ ሰልፎችን ማድረጋቸውም ግልጽ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በመግለጫ ጋጋታቸውና በተቃውሞ ሰልፍ ሱሰኝነታቸው ለውጥ ማምጣት ባለመቻላቸው ቅያሜ የገባው ነፃ ነኝ የሚለው ፕሬስም ቅያሜውን *ያለተቃውሞ ሰልፍ ህገመንግስቱ ህይወት አይኖረውም´* በሚል ክሱ የተቃዋሚ ፓሪቲዎችን ክስ እየደጋገመ ያሰማል፣ ስሙ እንጂ ፕሬስ፣ ስራው ገና ከመንገደኝነት አስተሳሰብ አልወጡም።

(የብዙዎቹን ነፃ ፕሬሶቻችንን የማንነትና የሽብርተኝነት ታሪክ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ታህሳስ 30 2006 ጥናት ይመልከቱ።) *ፓርቲዎቹ ከሰላማዊ እንቅልፍ ለመንቃት በርካታ አማራጮች ቢኖራቸውም በአንድ አማራጭ ላይ ተጣብቀዋል።´* በማለት ከላይ በተመለከተው የቀለም አብዮት ጽንሰ ሃሳብና አፈፃፀም መሰረት በተቃውሞ ሰልፍ ህገመንግስታዊ መብት ሽፋን አማራጭ የሆኑ የቀለም አብዮት መንገዶችን እየመከረ ነው። ለዚህ ደግሞ ጥሩና የቅርብ ማሳያ ሆኖ መቅረብ የሚችለው በነፃ ፕሬስ ህገመንግስታዊ መብት ሽፋን በየሳምንቱ ለህትመት የሚበቃውና ለቀለም አብዮት የሚተጋው ኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ነው።

"ያለተቃውሞ ሰልፍ ህገ-መንግስት ህይወት አይኖረውም" በሚል ርዕስ የመድረኩን ሰልፍ ተከለከልኩ´ አጀንዳ በሰሞኑ ዘገባው ለመተንተን የሞከረው ይህ ጋዜጣ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የብሔር ብሔረሰብን መብት ላስከበረ ብቻ ሳይሆን የህገ መንግስት እስትንፋስ በነፃ መቃወም፣ በነፃ ሃሳብን መግለጽ፣ በነፃ መንቀሳቀስ እና ሌሎችም መብቶች ማክበርን ያጠቃልላል።´ በማለት ያልበላውን ሲያክ ተገኝቷል።በመሰረቱ ህገመንግስቱ የኢትዮጵያ

ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሉዓላዊ መብት መገለጫ እና እስትንፋስ መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ የቀለም አብዮት አራጋቢው እንዳለው እና ከላይ በተመለከተው መሰረት ህገመንግሰቱ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ማስከበሩን ካመኑ፤ ብሄር ብሄረሰቦች ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች እንጂ ሌሎች ባለመሆናቸው መልሰው እንደገና ነጠላ መብቶችን እያነሱ ማንኮራፋታቸው የተጠየቅ ችግር ብቻ ሳይሆን በቀለም አብዮት መናወዝና መደንዘዛቸውን ያጋልጣል። እርስ በእርስ የሚጣረስ ሃሳብ ያሰፈረው ይኸው ጋዜጣ በቅርቡ በዩክሬንና በታይላንድ የታዩትን የቀለም አብዮቶች ተቃዋሚዎች ወይም እነ መድረክ በኢትዮጵያም እንዲደግሙት ምክር ለግሷል።

ከዚህ ምክር ባሻገርም ከላይ በተመለከተው የቀለም አብዮት ጽንሰ ሃሳብ መነሻ መሠረት Written demonstration (Residence demonstration)፣ ራስን ማጥፋትና ራስን ማቃጠል እንዲሁም የረሃብ አድማዎችን (Self immolation)፣ ከቤት አለመውጣትና ነገሮችን ወሮ የመያዝ (Direction demonstration  and occupation)፣ ታክስ አለመክፈልና ለመንግስት አለመታዘዝን (protesting government) . . . የመሳሰሉትን የቀለም አብዮት መንገዶች በህገመንግስታዊ መብቶች ሽፋን እንዲጠቀሙባቸው ጋዜጣው ምክሩን አስፍሯል።

እነዚህ መንገዶች ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲያዊና በምንም መመዘኛ ሰላማዊ የሚባሉ እንዳልሆነ የሚታወቅ በመሆኑ በህገመንግስታዊ መብቶች ሽፋን ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን መናድ እንደማይቻል ከመናገር ባለፈ ልንታገላቸው የሚገባ መሆኑን የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲገነዘቡት እንሻለን።